# የሁለት ትውልዶች ወግ

## ከቀይ ሽብር እስከ ሰሃራ

ከበልጅግ አሊ
ተከታታይ ታሪክ

<<ተሾመ ቶጋን ታውቀዋለህ?>>
<<ስሙን ሰምቻለሁ ማነው እሱ? >>አልኩት።
<<የፓርላማው አፈ ጉባዬ ነው። አንድ ቀን ታዲያ የመለስ ልጅ መጫወቻ ካልተገዛልኝ ብሎ አምርሮ ያለቅሳል። የወያኔ ባለስልጣናት በሙሉ ተጨንቀው መጫወቻ እየገዙ ይመጣሉ። ልጁ ግን ማልቀሱን አላቆመም። የወያኔ ባለስልጣናት ምን ዓይነት መጫወቻ ነው የምትፈልገው? ብለው ልጁን ይጠይቁታል።ልጁም እኔ የምፈልገው ተሾመ ቶጋን ነው ብሎ መለሰ። እነ ስብሀት ነጋ ልጁን አትቀልድ እሱን አታገኝም። እሱ የአባትህ መጫወቻ ነው አሉት።>>

ይህንን ቀልድ የሰማሁት አካባቢዬ ከሚኖሩ ወጣቶች ነው።

ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የሕዝብ ፣የሀገር አኗኗር ወደታሪክነት መቀየሩ የማይቀር ነው ። አሁን የነበረው የሚደረገው ማንኛውም ክስተት በሚገባ ተፅፎ ካልተቀመጠ ወደ አፈ ታሪክነትና ጭብጡን የለቀቀ ተረት ተረት መቀየሩ የማይቀር ነው። አፈ ታሪክ ደግሞ እውነትም ውሸትም ሊሆን ይችላል። በአገራችን ውስጥ የተፈፀሙትም አኩሪም ይሁን አዋራጅ ተግባሮች በማስረጃ በተጨበጠ ሃቅና ማስረጃ በመፀሐፍ ሰፍረው ሲገኙ ነው አንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ትውልድ የሚስተላልፋቸው።በሃገራችን ውስጥ እስከ አሁን የተፃፉ ሁሉ ትክክል ታሪክ ናቸው ብዬ ለመናገር ይከብደኛል። በተለይ በአሁኑ ጊዜ ወንጀለኞችና በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ አሳፋሪ ምግባርን ያከናወኑ አድርባዮች ታሪክን ለመበረዝ ቆርጠው ተነስተዋል። እንደዚህ አይነቱን ተግባር መዋጋት የእያንዳንዳችን ተግባር ነው ብዬ አምናለሁ። በዚህ ዓይነት ነው ተከታዩ ትውልድ ከሱ በፊት የነበረው ትውልድ ላይ የደረሰውን አሰቃቂ ጭፍጨፋዎች ሊውቃቸው የሚችለው።

ለምሳሌ ያህል በደርግ ዘመን የተፈፀመው ጭፍጨፋና የተከፈለው መስዋትነት በጥንቃቄ ሊዘጋጅና ለመጪው ትውልድ በቅርስነት ሊተላለፍ የሚገባው ታሪክ በሚገባ ሰላልተዘጋጀ በአሁን ጊዜ ወጣት የሆኑ መጠኑንና ጥልቀቱን ሊረዱት ኣልቻሉም። እንዲያውም አንዳንድ አድርባዮችና ሆዳሞች ታሪኩን ሲበርዙት ፣ ለእነርሱ በሚስማማ ሲቀይሩት ይታያሉ። ለሃገር መሞትን ሞኝነት አድርገው ለማስረዳት ጥረት ያደረጉም ይገኙበታል። የሚያስገርመው አሁን የፖለቲካ መሪ ነን የሚሉት ሳይቀሩ ይህንን አሳብ በተዘዋዋሪ ያጎለብቱታል።በሌላ በኩል ደግሞ የአሁኑ ወጣት አገሩን እንደማይወድ ሊጠቅሱ ይሞክራሉ።

የኢትዮጵያ ወጣቶች በደርግም ሆነ በወያኔ በሽብር ውስጥ እንደኖሩ የሚዘነጋ አይደለም። ደርግ ወጣቱን በቀይ ሽብር ከዛም በተለያየ ዘዴዎች በመቀጠል ወጣቱ ወደ ፖለቲካ እንዳይቀርብ ሲያደርግ ነበር። ወጣቱ ትውልድ ከቀይ ሽብር በኋላ ስለሀገራቸው ከማውራት ስለ ሌሎች ሃገሮች ብልጽግና እንዲያወሩ ተገደዋል። ይህ የሆነው ስለሀገር ማውራት የሚስገድል መሆኑ እርግጠኛ ሰለነበር ነው። ከዛም ወያኔ ስልጣን ላይ በመጣ ጊዜ ሽብሩ ቀጠለ እንጂ አልቆመም። የአሁን ወጣቶች እንደ ቀድሞ ወጣቶች ለሃገር ከመሞት ይልቅ ወደ ውጭ ሀገር መኮብለልን እንደ አማራጭ ይወስዱታል። ተምሮ ሀገር ውስጥ ሥራ አግኝቶ የተደላደለ ኑሮ ማግኘት የማይቻል መሆኑን ስለሚታወቅ ሌላም አማራጭ አልነበራቸውም።

ይህ ወጣቶችን በሽብር የማኖር ተግባር በግንቦቱ ምርጫ የታየ ነው። ወያኔ ለሃገራቸው ዕድገት ብለው ሰልፍ የወጡትን ወጣቶች በአደባባይ ገድሏቸዋል።ከሁሉ የሚገርመው ግን የግንቦቱን ንቅናቄ የሚመሩት ከነበሩት ውስጥ አንዳንዶቹ እንደተለመደው እነዚህን ወጣቶች ክደው ከወያኔ ጋር ሲተቃቀፉ ታይተዋል። የተሰውት ወጣቶች አይን ሳይፈስ እነ በየነና እነ ዶክተር ብርሃኑ ትግሉ እንዲቆም ሲታገሉ ነበር። ይህን ዓይነት አፀያፊ ተግባር ወጣቱን ከትግሉ ቢያርቀው የሚገርም አይሆንም።

ይህንን ፅሁፍ ለመፃፍ ስነሳሳ በአሁኑ ወቅት በወጣትነት እድሜ ውስጥ ያሉት ምን ያህል መስዋትነት እንደሚከፍሉ ብዙዎቻችን የምናውቅ አይመስለኝም። በሚከፍሉት መስዋትነት ዓላማ ላይ ልንስማማም ላንስማማም እንችላለን። ምክንያቱንም በተለያየ መንገድ ልንተነትነው እንችላለን። ችግሩ ግን አገራችን በተከታታይ  ከምትገኝበት የፖለቲካ ፣ የሶሻል ፣ የኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ነው። የወያኔና የሻቢያ የዘር ፖለቲካ በወጣቶቹ ላይ የፈጠረው ተስፋ መቁረጥ ከፍተኛ ነው። በተለይ ደርግ በሕብረተሰቡ ውስጥ ጥሎት የሄደውን ሽብር ለመቀየር ገና ብዙ ጊዜ የሚወስድ ነው። ከደርግ በኋላ የመጣው ወያኔም ያንን ሽብር በመቀጠል ወጣቱ ሀገሩ ውስጥ ለመኖር ያለውን ፍላጎት አሟጦታል እንጂ አላሻሻለውም። ስለዚህም ወጣቱ ከሀገሩ ለመውጣት የሚከፍለው መስዋትነት ግዙፍ ነው።

የምኖርበት አካባቢ በተለያየ መንገድ ወደ አውሮፓ የመጡ ወጣቶች አሉ። እድሜያቸው በሃያዎቹ አካባቢ ይሆናል። ታሪካቸውን ብዙ ጊዜ ስለሚያጫውቱኝ እነርሱን ሳገኝ ደስተኛ ነኝ። ከወጣቶቹ ጋር ምንም አማርኛ ብንነጋገር አንዳንዴ እነርሱ  የሚጠቀሙባቸውን ቃላቶች ስለማይገቡኝ ማብራሪያ እጠይቃለሁ።እነሱም ይተረጉሙልኛል። ጨዋታቸው ቀልዳቸው ሁሉ ይጥመኛል።የወጣትነት ዘመኔን ስለሚያስታውሰኝ እነርሱን ሳገኝ ደስተኛ ነኝ።

ከነዚህ ወጣቶች ጋር ተገናኝተን ያሳለፍነቻውን የሕይወት ገጠመኞች ስንጨዋወት ከላይ የጠቀስኩትን የእውነተኛ ታሪክ ለተከታይ ትውልድ ማስተላለፍ አለመቻል የሚያመጣውን የአስተሳሰብ መዛባት ልመለከተው ችያለሁ።  በቀይ ሽብር የተፈፀመውን ፋሽስታዊ ጭካኔ አንዳንዱን ለማመን ያዳግታችዋል። በወቅቱ የነበሩትን ወጣቶች ቆራጥነት ያደንቃሉ። ከወጣቶቹ ጋር ውይይታችን ሁል ጊዜ የሚጥም ነው። እነርሱ ከእኔ ስለ ኢሕአፓ ታሪክ መስማትን ይፈልጋሉ። እኔ ደግሞ ከእነርሱ ስለ ሱዳን ፣ስለ የቻድ በረሃዎች ፣ስለ ሰሃራ፣ ሰለ ሊቢያ፣ ሰለ ሜዲትራንያን ባሕር ፣ ስለ ጀልባ ፣ስለ ማልታ ፣ ስለ ኢጣልያን ፣ሰለ ቱርክ ፣ስለ ቡልጋሪያ ፣ ስለ ግሪክ ወዘተ  እንዲያጫውቱኝ እፈልጋለሁ።

ብዙ ጊዜ ሰለቀይ ሽብር እንድነግራቸው ይጠይቁኛል። አንዳንዴ አንግባባም። ብዙ ጊዜ የሚያነሱትን ጥያቄ መመለስ ያቅተኛል። የጊዜውን ልዩነት አጉልቶ ስለሚያሳየኝ እደነቃለሁ። ብዙዎቹ ወጣቶች ስለ ቀይ ሽብር ስነግራቸው ከቤተሰቦቻቸው ከሚሰሙት በስተቀር የጠለቀ ዕውቀት እንደሌላቸው ለመረዳት ችያለሁ ።ኢሕአፓ የታገለበትን ዓላማዎች አያውቁትም። አንዳንድ የሚያውቁት ነገር ቢኖር በሚኖሩበት አካባቢ ስለሚወራው ታሪክ ብቻ ነው።ያን ጊዜ እንዲህ ተደረገ፣ ወጣቶች እንዲህ አደረጉ፣ ሰልፍ ወጡ ፣ እዚህ እናንተ የምትቆሙበት ቦታ ላይ የእገሌ ሬሳ ወድቆ ነበር ፣ እዛ ጋ እገሊት ተጥላ ነበር ፣ እንደዚህ ዓይነት ንግግሮችን ያዳምጡ እንጂ ምክንያቱን ጠልቅው አያውቁም ነበር።

ስለዚያ ብዙ መስዋትነት ስለከፈለ ትውልድ ጠልቀው አለማወቃቸው በተለያየ ምክንያት ነው። ቀደም በደርግ አሁን በወያኔ ኢሕአፓ እንደ ጠላት ተፈርጆ ይገኛል። በተቃዋሚው ጎራም በግል መታወቅ የሚፈልገው ዲስኩሩን የሚጀምረው ያንን ትውልድ በመውቀስ ነው።  ከወጣቶቹ እንደተረዳሁት በትምህርት ቤት ውስጥ የኢትዮጵያን ታሪክ በተለይም ቀይ ሽብርን በሚመለከት ምንም ዓይነት ትምህርት እንደማይሰጥ ልረዳ ችያለሁ። በመረጃ በተደገፈ መልክ እውነቱ ተፅፎ አልተቀመጠም። ቢቀመጥም እነዚህ ወጣቶች እንዲረዱት ተደርጎ አልተፃፈም። ቀይ ሽብርን በተመለከተ ከጠየቁኝ ውስጥ አንዱ ጥያቄ ላይ ልንግባባ አልቻልንም። ብዙ ተወያይተንበታል።

<<ተወልዳችሁ ባደጋችሁበት አዱ ገነት ውስጥ እንዴት እጃችሁን ሰጥታችሁ ትገደላላችሁ? አታሳብሩም (አትጠፉም)እንዴ? >> ነበር ጥያቄው።ከዚህ ጥያቄ የምንረዳው ወጣቶቹ በሃገራችን ለተፈጠረው ችግር ሁሉ መፍትሄው ማሳበር (ከሃገር መውጣት) መሆኑን ነው የሚምኑት።

<<እኛ እንደ እናንተ መጥፋት፣ ከሃገረ መውጣት መፍትሔ ነው ብለን አናምንም ነበር። ሕዝባዊ መንግሥት ቢኖር ችግራችን የሚፈታ መሆኑን ነው የምናምነው። ያም ሆኖ ግን እዛው አዲስ አበባ ውስጥ ለመጥፋት ይሞከር ነበር። ቢሆንም ወዴት ይጠፋል። ዙሪያው በሙሉ እኮ መሄጃ የለም። አዲስ አበባ ሁሉም ቦታ በፋሽሽቶች ተሞልታለች።የኢሕአፓ መዋቅራችን ተሰባብሩዋል። ከመካከላችን ከደርግ ጋር የሚሰሩ አንጃዎች ተፈጥረው ነበር ። እነርሱ ይከታተሉናል። ነፃ እርምጃ እየተካሄደ ነበር።>> ልኳቸው።

<< ነፃ እርምጃ ማለት ምን ማለት ነው?>> ብለው ጠየቁኝ።

ነፃ እርምጃ ማለት በመኪና ውስጥ ሆነው የደርግ የምርመራ ክፍል ሰራተኞች ፣ከኢሕአፓ ውስጥ ከወጡ አንጃዎች ጋር በመሆን አዲስአባ ውስጥ እየዞሩ የኢሕአፓ አባል የመሰላቸውን በአውቶማቲክ መሣሪያ ጥይት እያርከፈከፉ የሚገሉበት ሁኔታ ነው። ወጣቱ ምን ይሁን ምን ለእነርሱ ጉዳያቸው አደለም። የኢሕአፓ አባል ከመሰላቸው ይገድሉታል።ከዛም ቀይ ሽብር ተጀመረና ብዙዎቻችን ታሠርን። ከዛ በኋላ በየመንገዱ እየገደሉ ይጥሉን ጀመር። በተወለደንበት ሠፈር ውስጥ ሬሳችንን ጣሉት። አባትና እናት የተገደሉ ልጆቻቸውን መንገድ ላይ ወድቀው አገኙ። ምንም መሄጃ ቦታ አልነበረም።

አዱ ገነት(አዲስ አበባ) ውስጥ መጥፋት ከበደ? ብለው ጠየቁኝ።ሕፃን ልጅ ተኮላትፎ ወላጆቹን እንዳሳቀ በፍቅር እየተመለከቱኝ በማይምነቴ ተዛበቱብኝ። ደነገጥኩ። ነገር ግን ወዲያው በወጣቶቹ አስተሳሰብ ከአንድ ሠፈር ወደ ሌላ መሄድና መደበቅ የሚቻል ነው የመሰላቸው። ቀይ ሽብር በመላ ሀገሪቱ ፣ በጠቅላላው ሕዝብ ላይ የታወጀ ግድያ መሆኑን አልተገነዘቡትም ነበር።

ለምን? ብዬ ጠየቅኋቸው። አንደኛው ጉሮሮውን በሳል አፅድቶ እንዲህ አለኝ።

<<የእናንተ ጊዜ የደረሰባችሁ የሚያሳዝን ነው። ነፃ እርምጃ አሁንም እኛ በየቀኑ አሁን በጭላዎቹ (በወያኔ ) ጊዜም እየኖርነው ነበር። በእናንተ ጊዜ ወግ ያለው ሞት ነበር። እኛን እኮ ተቃዋሚ ከመሰልናቸው ሌባ ነው ብለው ነው የሚጠብሱን (የሚገድሉን) አሁንም ቢሆን ልዩነት የለውም። እኛ ደግሞ አገራችን ውስጥ መኖር አንችልም። ሌላው እየበላ እየተዝናና እኛ ገና በወጣትነታችን የበይ ተመልካች መሆን ያስጠላል።ዛሬ ደልቶት የሚኖረው ዘመድ ውጭ ሃገር ያለውና ከወያኔ ጋር የተዛመደ ብቻ ነው። በተለይ ከውጭ ያለው ተመልሶ ሃገር ቤት መጥቶ ሲደሰት ስናየው እዛ ከመሰቃየት ማቅጠንን እንመርጣለን፡፡እናንተ ላይ የደረሰውን ከሰፈር እንሰማለን።ፖለቲካ ውስጥ መግባት የሚያመጣውን ችግር እንረዳለን።እናንተ የታገላችሁት ለአርሶ አደሩ ፣ ለላብአደሩ ነው ብለኸናል። እኛ ግን እራሳችን ለራሳችን ነው የምንታገለው።ለእኛ የሚታገልልን የለም። ስለዚህም እናሳብራለን(ከሀገር እንጠፋለን)። ለምሳሌ እኔን እይ። አንተ አዲስአባ ውስጥ መሄጃ አጣን ትላለህ።ልብ ብለህ ስማኝ።>>

<<ከአዱ ገነት እስከ ሱዳን ያለው ተወው እሱ አልጋ ባልጋ ነው።ከሱዳን ለእሬዎች( ኤርትራውያን) ከፍለናቸው ወደ ሊብያ ሊወስዱን ተነሳን።በአንድ ቶዮታ ፒክ አፕ መኪና ላይ የተጫንነው ሰላሳ ሶስት ነበርን። ከመካከላቸችን ዘጠኙ ሴቶች ነበሩ።ሌላ አንድ ቶዮታ መኪና አብሮን ነበር ። ግን እዛ መኪና ላይ የተጫኑት ወንዶች ብቻ ነበሩ።ሰሀራ በረሃን አቋርጠን ሊቢያ ለመድረስ ነበር። ስለ ሰሃራ የምታውቅ ይመስለኛል። ከአሸዋ በስተቀር ምንም የማይገኝበት ነው። ውሃ ፣ዛፍ ፣ ማረፊያ ፣ መጠለያ ፣ በፍፁም የለም። የምንጠጣው ውሃ እየተቆጠበ ነው የሚሰጠን ለዛውም ውሃው ውስጥ ብዙ እንዳንጠጣ  ቤንዚን ይጨምሩበታል። ጋሼ ጉዞው በጣም የሚያስመርር ነው። ግን አላማችን አውሮፓ መድረስ ስለሆነ ቆርጠን ነው የተነሳነው። ሰሃራ በርሀ ውስጥ አንድ ቀን ከተጓዝን በኋላ የቻድ ጥቁሮች እየተኮሱ መጡና ያዙን።ጭንቀት በመካከላችን ሰፈረ። ሴቶቹ ማልቀስ ጀመሩ።ወንዶቹ ተጨነቅን። ስለምናልመው የአውሮፓ ኑሮ ማሰብ ቀርቶ ስለ ሰሃራ ውስጥ ተቀብሮ መቅረት አዕምሮችንን አጣበበው። ሁላችንም የያዝነውን እንድናስረክብ ተነገረን። አንዳንዶቹ ሰጡ። ብዙዎቻችንን ግን ከክረን(ደብቀን) ዝም አልን። ቻዶቹ ፍተሻ ጀመሩ። የመጀመሪያው ልጅ ላይ ገንዘብ አገኙ። ከመካከላችንን አውጥተው በጥይት ጭንቅላቱ ላይ መትተው ገደሉት። ከዛም ሁላችንም የደበቅነውን እያወጣን ሰጠን።  ከሱዳኖቹ ጋር ብዙ ከተጨቃጨቁ በኋላ ሴቶቹን አንድ መኪና ላይ ጭነው ይዘዋቸው ሄዱ ። የዛ ሰዓት የነበረው ለቅሶና ጩኸት ልነግርህ አልችልም። እህቶቻችንን ለዘላለም የዝሙት ባርነት ተወሰዱ። ሕይወት አስጠላን።ጋሼ መሄጃ ማጣት ማለት ያኔ ነው።>>

ሌላኛው ደግሞ ጀመረ። << ጋሼ በእናንተ ጊዜ የተፈፀመውን ለማመን ያዳግተናል። ቆራጥነታችሁ ቢያስደስተንም ለምን ከዛ ሃገር ለመጥፋት አለመሞከራችሁ ይገርመኛል። እኔ እንደማምነው ሸገር ከማንኛውም ደን የበለጠ ጥቅጥቅ ያለች ደን ነች። ሸገር ቢከፋህ የምትሸቅልባት ፣ ብትደሰት የምትዝናናባት ነች። የኔን ደግሞ ስማ ልንገርህ  ሰሃራን በቀላል አለ ችግር ነው የተሻገርኩት።ቻዶችም አላገኙንም። የሊብያውያንንም ዘረኝነት ችየው ነበር። ግን በጣም የተሰቃየሁት ሜዲትርያንያን ባሕር ላይ ነው። በፖፖ ውስጥ አሸዋ ላይ በተቀመጠ ኮንፓስ እየተመራን በአንድ አረብ መሪነት ነፋሱ ጥሩ ነው ተብለን ባንድ አሮጌ ጀልባ ከሱማሌ ፣ ከጋና ፣ ከናይጀርሪያ ፣ወዘተ ስደኞች ታጭቀንና ጉዞ ጀመርን። ጉዞችን ወደ ጣልያን ነበር።ትንሽ እንደተጓዝን ማዕበል ጀመረ። ጀልባዋ ትናወጥ ጀመር። የጀልባዋ ካፒቴን ችግር እንደገባ አወቅን። መፀለይ ተጀመረ። እንደ ድንገት ጀልባዋ በጣም ተናወጠች። ጩኸትና ለቅሶ

በረከተ። ሁላችንም መፀለይ ጀመርን። ሴቶቹ ማልቀስ ያዙ። እኛም መጮኽ ጀመርን። አንደኛው ልጅ በፍርሃት እየጮኸ ማልቀስ ጀመረ ። የጀልባዋ ካፒቴን የሚያለቅሰውን ልጅ ወደ ባሕሩ እንድንጥለው አዘዘን። ጣልነው። ልጁ ባሕሩ ላይ ሆኖ ይለምን ነበር።ከዚያም ካፒቴኑ የተወሰኑ ልጆች ወደ ባሕሩ እንዲጣሉ አዘዘ። ተጣሉ። ጋሼ ሁል ጊዜ ሰለቀይ ሽብር ስሰማ የሚገርመኝ ለምን እንዳላቀጠናችሁ ነው።አዱ ገነት አደለችም መደበቂያ የሌላት። ባሕር ላይ ብቻህን ስትጣል ዋና ሳትችል የሚረዳህ ሳይኖርወደ ባሕሩ ስትሰምጥ ነው መደበቂ የሌለው።እናንተን ለመውቀስ አይደለም ግን ለምን እንዳልጠፋችሁ አሁንም አይገባኝም። >>

<<እኔ ደግሞ በተራዬ ልንገራችሁ ብዬ ጀመርኩ።አዱ ገነት እንደናንተው እናታችን ነበረች ። ተወልደን አድገንባታል። መውጫ መግቢያዋን እናውቃለን ። ግን እኛ ላይ የደረሰውም ቀላል አይደለም። በሃገራችን የተዛባ ሥርዓትን በመቃወም በመደራጀታችን ፣ በመታገላችን ፣ነፃነት በመጠየቃችን እንደ አውሬ እየታደንን በአደግንበት ሰፋር ከቤታችን እየተወሰድን ስንገረፍና ስንገደል ነበር። ቀይ ሽብር በብዛት በኢሕአፓ አባላት ላይ ይደረግ እንጂ የኢሕአፓ አባላት ያልነበሩ በተለያየ ምክንያት ተገድለዋል። አዲስ አበባ ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ ኢትዮጵያ ውስጥ ነበር ይህ ግድያ የሚፈፀመው። ከአንዱ ሰፈር ስትፈለግ ወደ ሌላ ሰፈር መሄድ አይቻልም። ደርግ የደህንነት የሚለውን የስለላ መዋቅሩን በሃገሪቱ ውስጥ በሞላ ዘርግቶ ነበር። ምንም መንቀሳቀሻ አይገኝም። እናት ልጇን አሳልፋ መስጠት ትገደዳለች።አባት በግርፋት ብዛት የተደበቀ ልጁን አሲዞ እስከማስገደል የደረሰበት ወቅት ነበር። የነበረውን ሁኔታ አሁን ለመገመት ይቸግራችሁ ይሆናል። የማዕበሉንም ሆነ የቻድ ጥቁሮች ያደረጉት ተግባር የሚሳዝን ነው። ሁላችንም የደረሰብን አስቃቂ ታሪክ አለን። ጊዜውና ሁኔታው ይለያይ እንጂ ስቃዩ ሰቃይ ነው። >>

<<የእኔን እንውሰድ ቀኑ ቅዳሜ ነበር ባላሰብኩበት ሰዓት ቀበሌዎች ሰንጋ ተራ ጋ ያዙኝ ከዚያም አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ አሰሩኝ። አንድ ይግረም የሚባል ፋሽስት ነበር። እሱ ነው የያዘኝ። ጥቆማ ደርሶት ነው። በበነጋታው ዕሁድ ሸገር ውስጥ አሰሳ ነበር። አሰሳ ማለት ምን አልባት አታውቁም ይሆናል። አዲስ አበባ በሞላ በታንክና በከባድ መሳሪያ ተከባ አብዮት ጥበቃና ወታደሮቸ በየቤቱ እየገቡ ፍተሻ ማድረግ ነው። የዛን ቀን ወደ ደርግ ፅሕፈት ቤት ወሰዱኝ። ሰኞ ዕለት ወደ ወፌ ገለበጡኝ። ወፌ ማለት ታውቃላችሁ? ሁለት እጃችሁ በገመድ ይታሰርና ሁለቱ እግሮቻችሁ እንደተቀመጣችሁ በእጆቻችሁ መሐል ይደረጋሉ።በእግሮቻችሁና በእጆቻችሁ መካከል አጠና ይገባና ሁለት ሰዎች በግራና በቀኝ ሆነው ሲያንጠለጥሉዋችሁ እግራችሁ ወደላይ ጭንቅላታችሁ ወደ ታች ይዘቀዘቃል። ከዚያም ከፍ ያለ ቦታ ላይ ይሰቅሉዋችኋል ። እንዳትጮሁ አፋችሁን በጨርቅ ይጎሰጉሱታል። ከዚያም እንደ ጌሾ ወቀጣ ውስጥ እግራችሁን መቀጥቀት ይጀምራሉ። ይህን ጊዜ ነው መሄጃ ማጣት>> አልኳቸው።

<<ጋሼ አንተን በገዛ ሀገርህ ወፌ ከተው አስረው ያሰቃዩኽን ስናስታውስ ላንተ እናዝናለን። በሰሃራ በረሃ ውስጥ የቻድ ጥቁሮች አግኝተው ያሰርዋትና ለብዙ ጊዜ ከእነርሱ ጋር ቆይታ በኋላ ግን መንገድ አግኝታ ወደ ሊቢያ የመጣች አንዲት የአዲስ አበባ ልጅ ኩርፋ ውስጥ አግኝቼ ነበር። ኩርፋ ከሰሃራ በረሃ ቀጥሎ ሊቢያ ውስጥ የምትገኝ አንዲት አነስተኛ የሊቢያ ከተማ ነች። እዛ ቦታ ወደ ሰሜን ሊቢያ ለመጓዝ ከመነሳታችን በፊት አንድ ቤት ውስጥ ከሊቢያ ፖሊሶች ተደብቀን ነበር። ሌሊት ሌሊት ያቺ ልጅ በኃይል ትቃዣለች። ፍርሀት ስለሚሰማት ትቀስቀሰንና ጠብቁኝ ትለናለች።ከሁለት ወር በኋላ ጭንቀቷ እየበዛ መጣና እራሷን ለማጥፋት ትሞክር ጀመር። አንድ ቀን ታዲያ ደብዳቤ ጽፋልን እራሷን አጥፍታ አገኘናት። በድብቅ ስለምንኖር በድብቅ ከተሰቀለችበት አውርደን በድብቅ ቀበርናት። ለእናቷ የፃፈችው ደብዳቤ እስከ አሁን ትዝ ይለኛል። በደብዳቤው ላይ የደረሰባትን ስቃይ ጽፋ ነበር። የቻድ ጥቁሮች ሳህራ በረሃ ውስጥ ያገኙዋቸውና ይዘዋቸው ወደሚኖሩበት ስፍራ ይወስዶቸዋል። በየተራ እየተፈራረቁ ይገናኟቸዋል። ለብዙ ጊዜ አለ እረፍት የተለያዩ ወንዶች ይቀያየሩባቸዋል። ብዞዎቹ ሴቶች በድብደባው ብዛት ሕያወታቸው በዚያው ይጠፋል። አንዳንዶቹ አርግዘው በስቃይ ይገላገላሉ። ያም ሆነም ግን ወንዶቹ መፈራረቃቸው አይቀርም። በስንት መከራና ስቃይ ሕይወታቸውን በዚያው ውስጥ ይገፋሉ። ከዛ ማምለጥ የማይሞከር ነው። ከተቻለም ደግሞ ከዛ አምልጠው የመጡት ከፍተኛ ጭንቀት አለባቸው። እራሳቸውን ከማጥፋት ሌላ አማራጭ የላቸውም። ጋሼ ይህ ነው መሄጃ ማጣት።>> አለኝ።

<<እንደዚህ ዓይነት አረመኔያዊ ተግባር በእኛ ሀገር አልተደረገም ማለት አይደለም ብዬ ጀመርኩ። አዲስ አበባ ያሉ ቀበሌዎች ሁሉ ወደ እስር ቤትነት ተለውጠው ነበር። የቀበሌ ባለስልጣኖች በሙሉ የመግደል ሥልጣን ነበራቸው። በዛን ጊዜ የነበሩት እህቶቻችን የደረሰባቸውን ስቃይ ልታውቁት ይገባል።እነዚህ አረመኔዎች ብረት በብልታቸው ውስጥ እየከተቱ ያሰቃዩዋቸው ነበር። ጡታቸውን በሳንጃ

የተወጉ ብዙ ናቸው። እነዚህ ቦዘኔ የሆኑ አብዮት ጥበቃዎች በምርመራ ስም ከእስር ቤት እያወጡ እግርና እጆቻቸውን አስረው ይገናኙዋቸው ነበር። ከዚያም አሰቃይተው ይገሏቸዋል። እሬሳቸውንም መፈክር ጽፈው እየለጠፉ በተወለዱበትና ባደጉበት ሰፈር ውስጥ ይጥሏቸዋል። የአዲስ አበባ ምድር በደም የተበከለች ነች። ታሪካችንም የቋሸሸ ነው።>>

በመካከላቸው የምትገኘው ሴት ልጅ ደግሞ እንዲህ ብላ አለች።<<አይ ጋሼ አሁን ላለነው ወጣቶች እኮ የተለያየ ወንዶች አለፍላጎታችን ሲገናኙን ነው የኖርነው። ከዚያም ውጭ የምናውቀው ኑሮ ሰለሌለ ይህንን ተግባር  እንደ ወንጀልም አንቆጥረውም። ገና የወር አበባችን ሳይጀምረን ነው ለሽርሙጥና የምንዳረገው። በእናንተ ጊዜ ያሉት ሴቶች ክብራቸውን ይዘው ለሃገራቸው ሲታገሉ ስለሞቱ እንቀናባቸዋለን።  ለምሳሌ እኔን ውሰድ። እኔ አሚቼ ( አዲስ አበባ የተወለዱ ቤተሰቦቻቸ ኤርትራውያን የሆኑ ) ነኝ። አዲስ አበባ ነው ተወልጄ ያደግሁት። መለስና ኢሣያስ የተጣሉ ጊዜ ወደ አስመራ ቤተሰቦቼ ሲላኩ እኔም አብሬ ሄድኩ።ከቤተሰቤ ተለይቼ አዲስ አበባ ልቅር ብል የሚጠብቀኝ ሴተኛ አዳሪነት ነው።ይህ ለመወሰን የተገደድኩት ገና የአስራ ሶስት አመት ወጣት በነበርኩበት ጊዜ ነው። ወደ አስመራ ለመሄድ እኔ ወስንኩ ትልልቅ ወንድሞቼና እህቶቼ ግን ለመሄድ ሰላልፈለጉ ቀሩ። እኔ ገና ኤርትራ ከመድረሳችን እንኳን ከሕዝቡ ከዘመዶቻችንም መስማማት አልቻልኩም። ደበረኝ ፣ደበተኝ ።ያም ሆኖ ሦስት ዓመት በጭንቀት ኖርኩ። አንድ ቀን ታዲያ ሻቢያ ጠረጋ(አሰሳ) ጀመረ። ለሳዋ(ኤርትራ ውስጥ የሚገኝ የወታደር ማሰልጠኛ ) ወጣቶችን  ፍለጋ ይዘው ነበር።ቤተሰቦቼ የዛን ቀን እንድደበቅ ነገሩኝ።ለእኔ ግን ያ ቀን የመወሰኛዬ ቀን ሆነ ።ቆረጥኩ። አዱ ገነት መመለስ አለብኝ። ከሀገሬ ማንም ሰው ሊያሰወጣኝ አይችልም ብዬ ደርምሼው መሄድ አለብኝ ብዬ ወስንኩ። አቀጠንኩ (ተጓዝኩ) በአስራ አምስት ቀኔ  በጎንደር አድርጌ አዱ ገነት ገባሁ።

<<እኔ ግን ወያኔ እንድኖር በከለከለኝ አዲስ አበባ ውስጥ ማንም ሳይከለክለኝ ተዝናኝቼ ኖርኩ። ወደ ኤርትራ ቤተሰቤ በወያኔ መላኩን የሚያውቁ ጎረቤቶቻችንን ከተመለስኩ በኋላ አግኝተውኝ ያውቃሉ። ግን ማንም ለወያኔ አሳልፎ  የሰጠኝ የለም።ኤርትራዊ ኢትዮጵያዊ የሚለውን ያመጡት ወያኔዎች ናቸው እንጂ ሕዝቡ አደለም። እኛ አብረን ተወልደን አብረን ያደግን ነን።ሌላም ቋንቋ አላውቅም አማርኛ ብቻ ነው የማውቀው።ከወያኔዎቹ  የተሻለ አማርኛ እናገራለሁ። በድብቅ አዲስ አበባ ውስጥ መሸቀል ጀመርኩ።ያ እጠላው የነበረውን ሴተኛ አዳሪነት በአስራ ስድስት አመቴ ጀመርኩ። ከብዙ ጨካኝ ወንዶች ጋር ተኛሁ። አሁን ኤድስ በበዛበት ጊዜ ኮንዶሙን ካላወጣሁ ብሎ የሚደባደብ ስንት አለ መሰለህ።በመጨረሻም በሸቀልኩት ገንዘብ ተጠቅሜ ወደ አረብ ሀገር ሰው ቤት ለመቀጠር ሄድኩ። የሄድኩት ቤይሩት ነበር። እዛ ሰው ቤት ተቀጥሬ ነበር የምስራው።እዛስ ምን እንደሚገጥመን ታውቃለህ። ለእመቤቲቱ ገረድ ፣ ለባልየው ደግሞ ጭን ገረድ ነው የሆንኩት። እዛም ቢሆን አረቦቹ እየተፈራረቁ ነው የሚጫወቱብን። አንድ ቀን ባልየው እንደለመደ እኔ ጋ እንደመጣ ሚስቱ ደረሰች። ከዛ ቀን ጀምሮ ያ ቤት ሲዖል ሆነ። እኔም እየከበደኝ መጣ። ሚስትየዋ ቀኑዋን ጠብቃ እንደምትገለኝ አወቅሁ።  በየቀኑ በእንደዚህ አይነት መኖር  እየደወከኝ( እየሰለቸኝ) መጣ። ወደ አውሮፓ ማቅጠን እንደለብኝ ተረዳሁ። እሁድ እሁድ አበሾች የምንገናኝበት ቤተክርስትያን አለ።አውሮፓ እንዴት መሄድ እንደሚቻል  ከዛ ጠየቅሁ። ወደ ግሪክ 375 ዶላር ተከፍሎ መሄድ እንደሚቻል ነገሩኝ። ነገሩ ሁሉ ቀላል መስሎ ታየኝ።ወሰንኩ። ገንዘቡን ለሚመራኝ መሪ ማፍያ ከፍዬ ጉዞዬን ጀመርኩ።>>

ጉዞዬን የጀመርኩት ከሊባኖስ ዋና ከተማ ከበይሩት ወደ ሶርያ ነው።

ይቀጥላል።

በሚቀጥለው ጊዜ አስደናቂ የሆኑ ጉዞዎችን ለአንባብያን ለማቅረብ እሞክራለሁ።ይህንን ፅሁፍ በሚመለከት ሀሳብ መስጠት ለምትፈልጉ በዚህ ኢሜል አድራሻ ተጠቀሙ።
beljig.ali@gmail.com